# የህብረተሰብ ተሳትፎ ና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ከከተማ እስከ ብሎክ ድረስ ያሉ ሥራዎች አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ

2014 ዓ/ም <u>አዲስ አበባ</u>

# መግቢያ

1

- ከተማችንውስጥበሚካሄዱየአገልግሎትአሰጣጥስራዎች፣የልማትእንቅስቃሴዎች፣የህገወጥነትመከላከልናሰላምማስፈንእናየበጎፈቃድአገልግሎትንማህበረሰቡበተሟላመልኩየሚያገኝበትእንዲሁምተሳታፊየሚሆንበትእናህብረተሰቡበሚኖርበትብሎክያሉትንችግሮችበመፍታትከመንግስትጋርበቅንጅትእንዲሰራ፣ችግሮችንበጋራእንዲፈታ፣ነጻናግልጽበሆነመልኩበማሳተፍለሁለተናዊለውጥወሳኝጉዳይበመሆኑ፤

2

- ***ህብረተሰቡበሚኖርበትብሎክያሉትንችግሮችበመፍታትየመንግስትመዋቅሩንበመደገፍእንዲሰራችግሮችንበጋራእንዲፈታነጻናግልጽበሆነመልኩማሳተፍለሁለተናዊለውጥወሳኝጉዳይነዉ፡፡***
- ***ተቋሙ ኮሚሽን ሆኖ ከመቋቋሙ በፊት የነበረው የአሰራር መመሪያ አሁን ካለው ተቋማዊ አደረጃጀትና የአሰራር ቅርፅ የተለየ በመሆኑና ይህም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዘርፍ በአዲሱ ጥናት መሰረት ከህብረተሰብ ተሳትፎ ጋር በመዋሀዱ  ቀድሞ ይጠቀምበት የነበረውን የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ አሁን ካለው አወቃቀር ጋር ማስተካከልና ማሻሻል በማስፈለጉ፤***

3

- በመሆኑምኮሚሽኑሕዝቡንበየደረጃውማሳተፍ፤የህዝብንምየልማትእንቅስቃሴዎችመደገፍእንዳለበትበመታመኑእናይህንተግባራዊየማድረግተቋማዊኃላፊነትያለበትበመሆኑነዋሪዎችስለከተማዉየሚወሰኑጉዳዮችንበሚመለከትመረጃየማግኘት፣ሀሳብናጥያቄየማቅረብመብታቸዉንእንዲጠቀሙለማስቻልሠላምናፀጥታውየተጠበቀበትአካባቢእንዲኖርእንዲሁምየብሎክነዋሪውበበጎፈቃድአገልግሎትየነቃተሳትፎየሚያደርግበትአናዜጎችበራሳቸውመልካምፍቃድእናተነሳሽነትውስጣቸውከሚሰማቸውሰብአዊአመለካከትተነስተውበከተማቸንማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊእናፖለቲካዊእድገትጊዜያቸውን፣ገንዘባቸውን፣እውቀታቸውንእናበጎአመለካከታቸውንእንዲያውሉእንዲሁምየበጎፈቃድአገልግሎትባህልእናተደራሽነትንለማጎልበትየሚያስችልየአሰራርስርዓትመዘርጋትሲሆን፤



ማህበረሰቡበሰላም፣በል
ማትእንዲሁምበበጎፈ
ቃድስራዎችላይየአመ
ለካከትእናየአስተሳስብ
ለውጥእንዲያመጣናተ
ግባራዊእንዲያደርጋቸ
ውማስቻል፤
ዓላማ
ነዋሪዎችንበማሳተፍበከ
ተማውአስተዳደርየሚሰ
ጠውንአገልግሎትበእኩ
ልነት፣በግልፅነትእናበፍ
ትሀዊነትመርህመሠረ
ትእንዲያገኙማድረግ፤
በከተማውአስተዳደርየልማትእቅዶችናበአፈፃፀማቸ
ውሂደትነዋሪውንቁተሳትፎእንዲያደርግእናየልማቱ
ምፍትሀዊተጠቃሚእንዲሆንማስቻል፡፡
የበጎፈቃድባህልንበማህበረሰቡዉስጥማጎልበት፤
በከተማውአስተዳደርእናበብሎክበነዋሪውንቁተሳትፎ
በከተማውሠላምናፀጥታእንዲሰፍንማስቻል፡፡

# መርሆዎች

1/መዋቅራዊየብሎክአደረጃጀትእናየህግማዕቀፍበማዘጋጀትህብረተሰቡንተሳታፊናተጠቃሚ ማድረግ፣

2/የሀብትአሰባሰብስርዓቱንበጠበቀመልኩሀብትንበማፈላለግወደስራበማስገባትየሀብትብክነትእንዳይኖር ያስችላል፡፡

3/የበጎፈቃድአገልግሎትለህብረተሰቡጠንካራማህበራዊመስተጋብርመፈጠርእናየበጎነትባህሉከጊዜወደጊ ዜእያደገመምጣት፤

4/ቀልጣፋናውጤታምየአገልግሎትአሰጣጥበመስጠትየነዋሪውንመሰረታዊችግሮችንመፍታት፤

5/ህገወጥነትንበመከላከልየብሎኩንሰላምናፀጥታማስጠበቅየሚያስችልየካውንስልአደረጃጀትንበመዘር ጋትሊፈጠሩየሚችሉትንህገወጥናአዋኪድርጊቶችንለመቀነስእንዲሁምነዋሪውበሰላምወጥቶበሰላምየ ሚመለስበት፤ደህንነቱየሚጠበቅበትስርዓትንመዘርጋትያስችላል፡፡

# የኮሚሽኑ ዋና ዋና አጀንዳዎች

1/የአካባቢ መሰረተ ልማት

2/የህገወጥነት መከላከልና ሠላም ማስፈን

3/የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

4/የአገልግሎት አሠጣጥ

# አጭር ርዕስ

1. **“ከተማ”:** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነዉ፤

2. **“ከተማ አስተዳደር”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዉ፤

3. **“ከንቲባ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነዉ፤

4. **“ካቢኔ”** ማለት የከተማው አስተዳር ካቢኔ ነዉ፤

5. **“ብሎክ”** ማለት በአንድ በመንገድ እና በወንዝ በተከለለ ሰፈር በተከታታይ የሚኖሩ ነዋሪዎች ያሉበት አነስተኛው መዋቅር አካል ሲሆን ከ50 እስከ 150 አባወራ ወይም እማወራ የያዘ እና በጋራ መኖሪያ ቤቶች ደግሞ በአንድ ፓሪሰል ዉስጥ ያሉ እንደ አንድ ብሎክ የሚቆጠር ነው፤

# የቀጠለ...

6."**ኮሚሽን**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ነው፤

7.“**ሰው**” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

8.“**የብሎክ ካውንስል**” ማለት 8 አባላት ያሉት ሆኖ በብሎክ ውስጥ የአስተሳሰብና የአኗኗር አንድነትና ውህደት ያላቸውን ነዋሪዎች ማዕከል ያደረገ ፤የአገልግሎት አሠጣጥ፣ የአካባቢ መሠረተ ልማት፣ የህገወጥነት መከላከልና ሰላም ማስፈን እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚያከናውን ነው ፡፡

# የካውንስሉ አደረጃጀት

በየደረጃው ስራዎችን የሚያስተባብሩ እና ውሳኔ የሚሰጡ  አካላት  ከዚህ በኋላ " ካውንስል "እየተባሉ የሚጠሩ ሲሆን በዚህ መሠረት፡-

1.የከተማ ካውንስል

2.የክፍለ ከተማ ካውንስል

3.የወረዳ ካውንስል

4.የብሎክ ካውንስል ናቸው፡፡

# ስለ አስተባባሪ ካውንስል አደረጃጀት

- በየደረጃው ስራዎችን የሚያስተባብር አስተባባሪ ካውንስል ከዚህ በኋላ "**ካዉንስል**" እየተባለ የሚጠራ ሲሆን በዚህ መመሪያ የተደራጀ ሆኖ የካዉንስሉ አባለት በከተማዉ ከንቲባ ሲታመንበት በተጨማሪነት ሊካተቱም ሆነ ሊቀነሱ ይችላል፤

የብሎክ ካዉንስል አባላት በቀጥታ በነዋሪው የሚመረጥ ሲሆን ብዛቱ ስራውን ለማስተባበር እንዲያመች ፰(ስምንት) ሆኖ የተደራጀ ሲሆን አባላቱም፡-

1. ዋና ሰብሳቢ፣
2. ምክትል ሰብሳቢ እና የኢኮኖሚ ዘርፍ አስተባባሪ፣
3. ፀሐፊ፣
4. ገንዘብ ያዥ
5. የማህበራዊና የአካባቢ መሠረተ ልማት ዘርፍ አስተባባሪ
6. የአገልግሎት አሰጣጥ (የመልካም አስተዳደር) ዘርፍ አስተባባሪ፣
7. የህገ-ወጥነት መከላከልና ሠላምና ማስፈን አስተባባሪ፣
8. የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስተባበሪ የሚያካትት

# 1/ዋና ሰብሳቢ

1 )በብሎኩ ያሉትን ተግባራት እንዲታቀድ ያደርጋል ፣በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፣

2) የብሎክ ካውንስሉን ይመራል፣ ያስተባብራል ፣ይደግፋል፣

3) የንብረት አያያዝ እና የሀብት አሰባሰብ ስርዓቱን ይከታተላል፣

4) ከወረዳው ካውንስሎች ጋር ተግባራትን ይገመግማል የሚነሱ ችግሮችን እንዲፈቱ ያደርጋል፣ መፈታታቸውን ለህዝብ ይፋ እያደረገ ይሄዳል፣

- 5) ለካዉንስሎች በተለያየ ተግባራት ዙሪያ ግንዛቤና ስልጠና እንዲሰጣቸው ያስተባብራል፣
- 6) ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ አካላት እንዲለዩ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣
- 7) በወረዳው ባሉ ሴክተሮች እና በብሎክ ካውንስሎች መካከል ቀረቤታ እንዲኖር እንዲሁም ሁሉም ተግባራት በብሎክ በመከወን በፍትሃዊነት ይሰራል፣
- 8) ሪፖርት ለሚመለከተው አካል አዘጋጅቶ ያቀርባል

# 2/ምክትል ሰብሳቢ እና የኢኮኖሚ ዘርፍ አስተባባሪ

- 1)ዋና ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ሰብሳቢን ተክቶ ይሰራል፡፡
- 2) በየብሎኩ የሚኖሩ የስራ አጥ ቁጥር በአግባቡ እንዲለዩ ያስተባብራል፣
- 3) የስራ ዕድል ፈጠራው በየብሎኩ እንዲሆን ያስተባብራል፣
- 4) በንግድ ዘርፉ የሚከሰተውን ህገወጥነትን ነዋሪው ራሱ እንዲከላከል የማስተባበር ስራ ይሰራል፣
- 5) የገቢ አሰባሰብ ስርዓቱ ፈጣንና በጊዜው የሚጠናቀቅ እንዲሆን በየብሎኩ የሚኖረውን ነጋዴ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት በወቅቱ ግዴታቸውን እንዲወጡ ያስተባብራል፣
- 6) ሸማቾች ከመንግስት እና ከህዝብ የተጣለባቸውን ሀላፊነት እየተወጡ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፣ የሚነሱ ጥያቄዎችን ከሚመለከተው አካላት ጋር በመነጋገር እንዲፈቱ ያስተባብራል፣
- 7) በእያንዳንዱ የኢኮኖሚ ዘርፍ ስራዎች ላይ ነዋሪው ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ያስተባብራል፣

# 3/ ፀሀፊ

- 1) እያንዳንዱ ተግባር በቃለጉባኤ እንዲያዝ ያደርጋል፣
- 2) የሚሰሩ ስራዎችን በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል በፅሁፍ ያስቀምጣል፣
- 3) ከካዉንስሎች ጋር በመተጋገዝ ስራዎችን በወረቀት ላይ ያሰፍራል፣
- 4) ሌሎች በካውንስሉ የሚሰጡትን ተግባራትን ያከናውናል፣

# 4/የማህበራዊና የአካባቢ መሠረተ ልማት ዘርፍ አስተባባሪ

- 1) በብሎኩ የሚሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎችን ይለያል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ በማድረግ እንዲፈቱ ያደርጋል
- 2) የሚሰሩ የአካባቢ መሰረተ ልማት ስራዎች በብሎኳ በፍትሀዊነት መሰራታቸውን ያረጋግጣል፣
- 3) በብሎኩ የሚኖሩ በጎ ፈቃደኞችን በማስተባበር በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ያስተባብራል፣
- 4) የአካባቢ ልማት ስራዎች ጥራታቸውን ጠብቀውና በወቅቱ እንዲጠናቀቁ ለነዋሪው አገልግሎት እንዲሰጡ

# የቀጠለ...

- 7) የተለያዩ በብሎኩ የሚገኙ ድርጅቶችን በማስተባበር ለአካባቢ መሰረተ ልማት ድጋፍ እንዲያርጉ ያመቻቻል ፣
- 8) የሚሰሩ የልማት ሥራዎች የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል ሙያዊ እገዛ የሚያደርጉ ባለሙያዎችን በየደረጃው ካሉት አካላት ድጋፍ ይጠይቃል፣
- 9) ለልማት ስራዎች የሚውሉ ሀብቶች በትክክል ስለመሰብሰባቸውና ወጪ ስለመደረጋቸው ያረጋግጣል፣
- 10) በብሎኩ ውስጥ የሚሰሩ የሕዝብ የልማት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

# የቀጠለ...

- 11) የብሎኩ ነዋሪ አካባቢውን ጽዱ እና ውብ እንዲያደርግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል ያሥተባብራል፣የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሰርዓቱ እንዲዘምን ነዋሪውን በማነሳሳት ተሳታፊ እንዲሆን የማስተባበር ስራ ይሰራል፣
- 12) ለአካባቢ ጤና ጠንቅ የሆኑ የመፀዳጃ ቤት እና ተመሳሳይ ፍሳሾች ወደ ጐርፍ ውሃ ማስወገጃ ቱቦና ቦይ ውስጥ የተያያዙትን በመከታተል የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ ስራዎች ያስተባብራል፣
- 13) በጤና አጠባበቅ ዙሪያ በብሎኩ እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በመገምገም ያሉ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ ያቀርባል፣ የተወሰደውንም እርምጃ ለነዋሪው ይፋ ያደርጋል፣
- 14) የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ትግበራ ሥራን ከብሎክ የልማት ስራ ጋር በማስተሳሰር ያስተባብራል፣ ይመራል፣

# የቀጠለ...

15) ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የተሳካ እንዲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፤

16) እድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናት ወደ ትምህርት ገበታ እንዲገቡና ትምህርት እንዳያቋርጡ የመለየት እና የክትትል ስራ ይሰራል፣

17) በመንግስት ድጎማ ለትምህርት የሚመጡ ግብዓቶች በአግባቡ ለህብረተሰቡ መድረሳቸውን ይከታተላል፤

20)የችግኝ ተከላና እንክብካቤ ላይ ነዋሪው እንዲሳተፍና ባለቤት እንዲሆን ያስተባብራል ግንዛቤ እንዲፈጠር ከሚመለከታቸው ሴክተሮች ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

21)በብሎኩ የእርስ በእርስ መደጋገፍ እንዲጠናከር ፣ማህበራዊመስተጋብሩ የተሳሰረ መደጋገፍና መረዳዳት ላይ ያተኮረ እንዲሆን ያስተባብራል፣

## 5/የአገልግሎት አሰጣጥ (የመልካም አስተዳደር) ዘርፍ አስተባባሪ

- 1) በሴክተሮች የሚሰጠውን የአገልግሎት አሰጣጥ ለሁሉም ነዋሪ በፍትሀዊነት እና በእኩልነት እንዲደርስ የውይይት መድረኮች ከሴክተሮች ጋር ይወያያል፣
- 2) በየብሎኩ የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ነቅሶ በማውጣት እንዲፈቱ ከሴክተሮች ጋር ስራዎችን ያስተባብራል፤
- 3) በሁሉም ደረጃ በሚገኙ ተቋማት ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎት እንዲሰጥ ያስተባብራል፣ስለ

# 6/የህገ-ወጥነት መከላከልና ሠላምና ማስፈን አስተባባሪ

- 1) በብሎኩ ለሰላም እና ጸጥታ ስጋት የሆኑ ድርጊቶችን/ቦታዎችን መረጃ ይለያል፣ያደራጃል፣ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣
- 2) የህገወጥነት መከላከል እና የሰላምና ጸጥታ ስራን ተግባራዊ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ይሰራል ፣ ያስተባብራል፣
- 3) ከብሎኩ ነዋሪዎች ጋር በመሆን በግምጃ ቤት ሊጠበቁ የማይችሉ ለልማት የሚውሉ ንብረቶችን ከስርቆትና መጥፋት የሚጠበቁበትን ሁኔታ ይቀይሳል፣ ንብረቶችን በተሰረቁ ወይም በጠፉ ጊዜ አጥፊዎች የሚታወቁበትንና ለሕግ ቀርበው አስፈላጊው እርምጃ ተወስዶ ንብረቱ የሚተካበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- 4) በብሎክ ውስጥ ህገ-ወጥ ተግባራትን የሚፈፅሙትን በመለየት ከህገ ወጥነት እንዲወጡ ተገቢውን ምክር እና ግንዛቤ ይሰጣል ፤በምክር የማይመለሱትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፣
- ፤
-

# የቀጠለ...

- 5) በብሎኩ የሚገኙ ነዋሪዎች የውጪ መብራት እንዲያወጡና እንዲያበሩ የግንዛቤ ስራዎችን ይሠራል፣ ያስተባብራል ፣
- 6) ህብረተሰቡን በማስተባበር በብሎኩ የሚገኙ መሰረተ ልማቶች ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ይሰራል ፣ያስተባብራል፣ይቆጣጠራል፣
- 7) የብሎክ ነዋሪዎችን በማስተባበር የጥበቃ ማማ መስራት፣ በቅጥር ጥበቃ አካባቢያቸው እንዲጠበቅ ይደግፋል፣ያስተባብራል፣
- 8) ከኮሚኒቲ ፖሊሶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፣
- 9) በብሎኩ ህገወጥ ተግባራትና ሰላም ማስፈን ስራዎችን የማስተባበር ነዋሪውን ያሳተፈ ስራዎች እንዲሰሩ ለማድረግ የሚያስችል ዕቅዶችን ያወጣል፣አፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል

# የቀጠለ…

- 10)የብሎክ ነዋሪዎች የሠላም ባለቤት እንዲሆኑ በየአካባቢያቸው በየተራ እንዲተብቁ ያስተባብራል፤
- 11)የብሎኩን አዲስ እና ነባር ነዋሪዎች መረጃ ይይዛል፤ለሚመለከተው አካልም ሲጠየቅ ያቀርባል፤
- 12)በብሎክ ውስጥ ለሠላምና ፀጥታ ስጋት እና አጠራጣሪ የሆኑ ሁኔታዎችን ሲያዩ ጥቆማ ይቀበላል፣ ይሰጣል፤
-
- 13)ህዝባዊ ፤ሀይማኖታዊ እና መንግስታዊ በዓላት እና ኩነቶች ላይ በሰላምና ፀጥታ ጉዳይ ላይ በንቃት ይሳተፋል፤ያስተባብራል፤
-
- 14) በብሎክ ውስጥ ያሉ መንደሮችን በማደራጀት የሰላምና ፀጥታ ስራዎችን እንዲተገብሩ የመደገፍና የማስተባበር ስራ ይሰራል፤

# 7/የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስተባበሪ የሚያካትት ይሆናል፡፡

1. የብሎኩን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተግባራትን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤
2. የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ባህል በብሎክ ነዋሪው ዘንድ ማጎልበት፣
3. በብሎኩ የበጎ ፈቃድ ተግባራት ዙሪያ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት ያቀርባል፤
4. በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚወጡ መመሪያዎችና የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ይደግፋል፣
5. የብሎኩን የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በአምባሳደርነት ያገለግላል፣

•
•
•
•
•

# የቀጠለ…

6.የበጎ ፈቃድ ማህበራት ትስስር እንዲፈጥሩ፤ ልምድ ልውውጥ እንዲያካሂዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

7.የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን የግንዛቤና ማነቃቂያ ፕሮግራሞችን በየደረጃው ካሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንዲካሄድ ያደርጋል፤

8.አጠቃላይ የብሎኩን የዕለት ተለት የበጎ ፈቃድ ተግባራት ያከናውናል፤

9.በብሎክ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑ ግለሰቦች/ተቋም መረጃ ይለያል፣ ያደራጃል፣ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣

10.የካውንስሉን የዕቅድና አፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፤ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣

11.የእውቅና፣ የማበረታቻና የሽልማት ፕሮግራሞችን እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

# 8/ገንዘብ ያዥ

- 1) ከሕዝቡና ከልማት አጋሮች /ባለሃብቶች ወዘተ/ ለልማቱ እና ለበጎ ፈቃድ ሥራ ማስፈፀሚያ የሚሰበሰበውን ገንዘብና ቁሳቁስ በሕጋዊ የአካባቢ ልማት ደረሰኝ ይሰበሰባል፣ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለተፈለገው ዓላማ እንዲውል ይደረጋል፣ ጥሬ ገንዘብን በተመለከተ በወረዳው ካውንስል በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ በየዕለቱ ገቢ ያደርጋል፣
- 2) ገቢ የተሰበሰበባቸውን ደረሰኞች፣ የባንክ ደረሰኞችና ክፍያ የተፈፀመባቸውን ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፣በእጁ የሚገኘውን የገቢና ወጪ ደረሰኞችን የሂሳብ ሰነዶችን በጥንቃቄ ይይዛል፣የባንክ ሳጥን /ካዝና/ ሂሳብን በአግባቡ በመመዝገብ እንቅስቃሴውን ይከታተላል፡፡
- 3) ከካዉንስሉ ጋር በመሆን ገቢ ማስገኛ መንገዶችን በመቀየስ በመመሪያው መሰረት ሂሳቡን ያንቀሳቅሳል
- 4) ሌሎች በካዉንስሉ የሚሰጡትን ተግባራትን ያከናውናል

# በየደረጃው ያለ ካውንስል ተግባርና ኃላፊነት

በየደረጃው ያለው ካውንስል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

- ✓ በተደራጁበት እርከን ያለውን የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራዎች በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤
- ✓ የኤጀንሲውን ዓላማ ለማስፈጸም የሚረዱ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤
- ✓ በየደረጃው ያለውን ካውንስል የሥራ ዕቅድ እና አፈጻጸም ይገመግማል፤አቅጣጫ ይሰጣል፣ ችግር ባለበት ማስተካከያ ይወሰዳል
- ✓ በህብረተሰብ ተሳትፎ የሚሰሩ ተግባራትን ይለያል፤ ተግባራዊ እንዲሆኑ ለኤጀንሲው ያስተላልፋል፤
- ✓ ሌሎች የህብረተሰብ ተሳትፎ የሚጎለብትበትን ስልት ይቀይሳል፡፡

# የፋይናንስ ምንጭ

ህብረተሰቡ
የልማትስራ
ውንለመሳ
ተፍ65በመ
ቶቀመርድጋ
ፍያደርጋል፣
ዝርዝሩበፋ
ይናንስመ
መሪያመሰረ
ትይፈፀማል
።

አስተዳደሩየ
ልማትስራ
ውንለመደገ
ፍ35በመቶ
ቀመርድጋፍ
ያደርጋል፣ዝ
ርዝሩበፋይ
ናንስመመሪ
ያመሰረትይ
ፈፀማል።

# የተሻሻለው የፋይናንስ መመሪያ

**መመሪያ**

ቁጥር 1/2014

# ትርጓሜ

- “የሕዝብ መዋጮ” ማለት መንግስት ከሚመድበው የበጀት ውጪ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪዎች ለአካባቢ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ፣ለቅጥር ጥበቃና ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማስፈጸሚያ የሚውል በጥሬ ገንዘብ፣ በዓይነት ፣ በጉልበት ወይም በሙያ የሚሰበሰብ ሀብት ነው፡፡ከመያድና ከልማት አጋሮች ባለሃብቶች ወዘተ የሚሰበሰበውንም ገንዘብና ቁሳቁስ ይጨምራል፡
- "ቀጠና" ማለት ከወረዳ በታች ከብሎክ በላይ ሆኖ ከ8 አስከ 10 የሚደርሱ ብሎኮችን የሚይዝ አደረጃጀት ሲሆን በዋናነት የነዋሪውን አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች

# ትርጓሜ

- “ከመንግስት የሚመደብ የድጋፍ በጀት” ማለት ለአንድ ወይም ለተለያዩ የልማት ፕሮጀክት ሥራዎች እንዲዉል ለወረዳ የተመደበ ካፒታል በጀት ነዉ፡፡
- “የኦዲት ካውንስል “ ማለት ለአካባቢ መሰረተ ልማት ፣ለቅጥር ጥበቃና ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተግባር ወጪ የሚደረጉና የሚሰበሰቡ ገንዘቦች፣ ቁሳቁሶች፣ ጉልበትና ዕዉቀት በትክክል ስለመሰብሰባቸዉ ወጪ ስለመደረጋቸዉ፣ ስለመመዝገባቸዉ፣ በስራ ላይ ስለመዋላቸዉ አሰራሩ በአስተዳደሩ የፋይናንስ መመሪያዎች መሰረት ስለመከናወናቸው የሚያጣራ የሚያረጋግጥ ሪፖርት የሚያደርግ ከህግ ዉጪ የሚሰሩትን በማቅረብ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ የሚያደርግ ነዉ፡፡

# ትርጓሜ

."ተወካይ" በተለያዩ ዘርፎች የሚሰማራ ማለትም ህዝብን በመቀስቀስ፣ ገንዘብና ንብረት በማስተዳደር ፣ስራዎችን በመከታተልና በመቆጣጠር ዘርፍ ላይ የሚሰማሩ ናቸው፡፡

." ቅጥር ጥበቃ" ማለት በብሎክ ጥበቃ ላይ የሚሰማሩ በሕብረተሰቡ መዋጮ ክፍያ የሚፈጸምላቸው ቅጥረኞች ናቸው፡፡

## ከነዋ ሪው ስለሚዋጣው እና ከመንግሥት ስለሚ መደበው "የድጋፍ በጀት" አሰባሰብና አስተዳደር

### ባንክ ሂሳብ የሚከፈትበት ሁኔታ

- ከሕዝብ መዋጮና ከመንግሥት የሚመደበው የድጋፍ በጀት የሚቀመጥበት መደቡ "A" የሆነ የባንክ ሂሳብ ከክፍለ ከተማው ፋይናንስ ጽህፈት ቤት በኩል ይከፈታል፡፡

# የቀጠለ…

**<u>የባን ክ ሂሣብን የማንቀሳቀስ ኃላፊነት</u>**

1) በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው መደቡ”A” የሆነ የሕዝብ መዋጮ ከመንግሥት የሚንቀሳቀሰው ለወረዳው ዋና ስራ አስፈጻሚ የክፍያ ሰነዱ ቀርቦ ውሳኔ ሲሰጥበት የወረዳው ጽህፈት ቤት ኃላፊ ከህብረተሰቡ የሚወከል እና የሂሳብ ሹም በጣምራ ከአንዱ ጋር ሲፈርም ይሆናል፡፡

2) በህገወጥነት መከላከልና ሰላም ማስፈን የአካባቢ ቅጥር ጥበቃ ሀብት አሰባሰብና ወጪ በአንቀጽ 4

# የቀጠለ...

**የ ደረሰኝ አያያዝና አጠቃቀም**

1) የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞቹን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮን በማስፈቀድ ኮሚሽኑ ያሳትማል፤ ለየክፍለ ከተሞች እንዲሰራጭ ያደርጋል፣

2) የክፍለ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤትም በሥሩ ላሉ ወረዳዎች ጥያቄያቸውን መሠረት በማድረግ ያሰራጫል፣ ለእያንዳንዱ ወረዳ ያሰራጨውን ደረሰኝ ብዛትና ንምራ ቁጥር ከ እስከ የተሟላ መረጃ መያዝ ይኖርበታል፣

3) ደረሰኞቹ ለገቢ መሰብሰቢያነት ሲያስፈልጉ የወረዳው ካውንስል በሚመድበው የሂሣብ ሹም አማካኝነት በደብዳቤ ሲጠየቅ ወጪ ተደርጎ እንዲሰጠው ይደረጋል፣

4) በወረዳው የተሰየመው ሂሣብ ሹም የተቀበለውን ደረሰኝ ለብሎክ ካውንስል ገንዘብ ያዦች ለእያንዳንዳቸው አስፈርሞ ያሰራጫል፣

# የቀጠለ...

5) በብሎክ እና በወረዳው ካውንስል በኩል ለህዝብ ለአካባቢ ልማት ፣ለቅጥር ጥበቃ እና ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተግባር ከህዝብና ከበጎ አድራጎት ሰጪዎች ለሚሰበሰብ ገንዘብ የአካባቢ ልማት የገቢ ደረሰኝ ሊቆረጥለት ይገባል፣

6) ከከተማ አስተዳደሩ ለህዝብ ልማት ስራ የሚሰጠዉ 35 በመቶ ገቢ ሲደረግ የአካባቢ ልማት ገቢ ደረሰኝ በወረዳዉ ጽህፈት ቤት በኩል መቆረጥ ይኖርበታል፣

7) እያንዳንዱ ጥራዝ/ፓዱ/ ተሰርቶበት ሲጠናቀቅ በጥራዙ የተሰበሰበውን ገቢ የባንክ deposit slip እና የደረሰኙን ሁለተኛ ቅጂ ጋር በሂሣብ ሹሙ ተገናዝቦ ትክክለኝነቱ ተመሳክሮ ፓዱ ላይ የቀረውን ኮፒ እንዳለ ለወረዳው ካውንስል ያስረክባል፣

8) የወረዳው ካውንስል ደረሰኝ የሚያሰራጨው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተገለጸው መሠረት አስቀድሞ የተወሰደው ደረሰኝ

# የቀጠለ...

9) የወረዳው ካውንስል የሂሣብ ሹም የተረከበውን የተሰራባቸው ደረሰኞች በጥንቃቄ በማስቀመጥ በየአመቱ በአዲስ አበባ ዋናው ኦዲተር ኦዲት ያስደርጋል፣ማናቸውም የሂሳብ ሰነዶቹም ለ10 ዓመት ያህል በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ያደርጋል፣
10) የወረዳው ካውንስል ገቢ የተሰበሰበባቸውን ደረሰኞች የባንክ ክሬዲትና ዴቢት አድቫይሶችን እና ክፍያ የተፈፀመባቸውን ሰነዶች በአግባቡ መያዝ ይኖርበታል፤ የገቢና የወጪ ደረሰኞችን፣ የሒሳብ ሰነዶች ፣የባንክ ሳጥን ወይም ካዝና ሂሳቦች በአግባቡ እንዲመዘገቡ ያደርጋል፣ እንቅስቃሴውንም ይከታተላል፣
11) የወረዳው ካውንስል የተሰበሰበውንና ወጪ የሆነውን ገንዘብ የከተማው የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ በሚያዘው መሠረት የወጪ መዝገብ በማዘጋጀት በወጪና በገቢ መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት፣
12) ለአካባቢ ልማት፣ለቅጥር ጥበቃና ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተግባራት የገንዘብ ወጭ ማድረጊያ ደረሰኝ የከተማው ፋይናንስ ቢሮ

# የቀጠለ...

13) ከህዝብ መዋጮ፣ መንግስት ከሚመድበዉ የድጋፍ በጀትና ከበጎ አድራጎት ሰጪዎች የተገኘዉ ገንዘብ ከ A አካዉንት ወጪ በሚሆንበት ጊዜ ለሚሰራዉ የቼክ መጠን መሂ7 (pv) በወረዳዉ ጽ/ቤት በኩል መሰራት ይኖርበታል፣

14) ከA አካዉንት ወጪ የሚደረጉ ክፍያዎች ሙሉ በሙሉ በወረዳዉ ጽ/ቤት በኩል መስተናገድ ይኖርባቸዋል፣

# የቀጠለ…

**<u>ገንዘብ ባንክ ማስገባትና ስለመመዝገብ</u>**

1) በብሎክ የተሰበሰበውን ገቢ የካውንስሉ ገንዘብ ያዦች በተከፈተው ”A” አካውንት በ24 ስዓት ዉስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፣

2) በ24 ሰዓት ገቢ የሆነበትን deposit slip አንድ ኮፒ እና የገንዘብ መሰብሰቢያውን ሁለተኛ ቅጂ ለወረዳው ካውንስል የሂሣብ ሹም ማስረከብ አለባቸው፣

3) በብሎክ እና በወረዳው ካውንስል ከህዝብና ከበጎ አድራጎት ሰጪዎች ለልማት ስራ ተሰብስበዉ ወደ A አካዉንት ገቢ ለተደረጉት ሂሳቦች በቀረበዉ የባንክ ዲፖዚት ስሊፕና የሁለተኛዉ ቅጅ የገቢ ደረሰኝ ተያይዞ ሲቀርብ መሂ 3 (SRV) በወረዳዉ ጽህፈት ቤት በኩል መቆረጥ

# የቀጠለ…

4) በወረዳዉ ጽህፈት ቤት በኩል ገቢ ሆነዉ ወደ A አካዉንት ገቢ ለተደረጉ ሂሳቦች በባንክ ዲፖዚት ስሊፕ መሰረት መሂ 7 (pv) ሊሰራላቸዉ ይገባል፣

5) የወረዳው ካውንስል ሂሣብ ሹም የተቀበለውን deposit slip መነሻ በማድረግ ለእያንዳንዱ ብሎክ የገቢ ተቀጽላ ሌጀር /subsidiary Ledger/ እና በአጠቃላይ ሌጀር /General Ledger/ ለይቶ በማዘጋጀት የሂሣብ ምዝገባ ያካሂዳል፡፡ይህ ማለት እያንዳንዱ ብሎክ የሰበሰበውና ገቢ ያደረገው

# የቀጠለ...

**<u>የ መንግስት የድጋፍ በጀት ስለሚ ለቀቅበት ሁኔታ</u>**

1) የከተማ አስተዳደሩ የሕዝብ የአካባቢ ልማት ስራ ከተሰበሰበዉ ገንዘብ ወይም ከጠቅላላዉ ወጪ 35% የሆነ በጀት በድጋፍ ማበረታቻ መልክ ይሰጣል፡፡

2) ከመንግሥት የበጀት ድጋፍ ገንዘብ የሚለቀቀው የላቀ የሕዝብ የአካባቢ ልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ተሳትፎ እውቅና እና ማበረታቻ ድጋፍ በመመሪያዉ በተገለፀው መሠረት ወረዳው በብሎኩ ከሕዝብ የተገባውን ቃል ሙሉ በሙሉ ማሰባሰቡን ሳረጋገጠባቸው ኘሮጀክቶች በጋራ ወይም በተናጠል ጥያቄ ቀርቦ በወረዳው ፋይናንስ ጽህፈት ቤትና በጽህፈት ቤቱ ተረጋግጦ በወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ አማካኝነት ለክፍለ ከተማው ቀርቦ ሲወሰን ይሆናል፡፡

3) የተወሰነዉን ዉሳኔ መሰረት አድርጎ ክ/ከተማዉ የመንግስት የድጋፍ በጀት እንዲለቀቅለት ለኮሚሽኑ ጥያቄዉን ያቀርባል፣

# የቀጠለ…

4) ኮሚሽኑ የበጀት ዝዉዉር ፎርም በመሙላት በጀቱ ለጠያቂዉ ክ/ከተማ እንዲዛወርለት ለፋይናስ ቢሮ ጥያቄዉን ያቀርባል፣ የፋይናንስ ቢሮም የበጀት ዝዉዉር ጥያቄዉን ካመሳከረ በኋላ ዝዉዉሩን ይፈጽማል፡፡

5)ከመንግስት የድጎማ በጀት ውስጥ ክፍለ ከተሞች ጠይቀው ከተፈቀደላቸው ውጪ የሚተርፈውን ገንዘብ በከተማው አስተዳደር ከሚገኙ በዝቅተኛ የገቢ ሁኔታ ላይ ካሉት ብሎኮች ውስጥ በመመልመል(በመምረጥ) በልዩ ሁኔታ በወረዳ ካውንስል እና በክፍለ ከተማ ካውንስል መረጃዎችን በማጥራት እና በማደራጀት ለኮሚሽኑ በማቅረብ የድጎማ በጀት(ማቺንግ ፈንድ) ለሚፈለገው ልማት የሚወስደውን በጀት በማረጋገጥ የሚደገፍበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ 6)የመንግስት የድጎማ በጀት ጥያቄ በዓመት ሁለት ጊዜ

# የቀጠለ…

**የ ዕቃና የአገልግሎት ግዥ አፈጻጸም**

1)መንግሥት ከሚመድበው የድጋፍ በጀትና ከሕዝብ መዋጮ የተገኘ ገንዘብ የሚፈጸም ግዥ የፋይናንስ ቢሮ ያወጣውን የከተማ አስተዳደሩን የግዥ አፈጻጸም መመሪያ የጠበቀ ይሆናል፣

2)የወረዳ ካውንስል የኘሮጀክት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የሚሆን ማንኛውም ግዥዎችና ክፍያዎች የወረዳው ጽህፈት ቤት ሲፈቅድ የከተማ አስተዳደር የመንግሥት የግዥ አዋጅና መመሪያ መሠረት በተፈለገው ጥራትና መጠን በፍጥነት ግዥውን ይፈፅማል፡፡ ከግዥ ውሎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች አፈጻጸሙን ክትትል ያደርጋል፣

3) በወረዳ ውስጥ በሚሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎችን በተመለከተ በኮሚሽኒ የሚቋቋመው የጨረታ ኮሚቴ ከ5 ያላነሰ ሆኖ ስብጥሩ ከንብረት አስተዳደርና ከግ¡ ኦፊሰር ውጪ ሆኖ ከፋይናንስ ግ¡ና ንብረት አስተዳደር በተጨማሪም በስራ ሂደቱ ያሉ የአባላቱ ቁጥር ከ5 ያነሰ ከሆነ የስራ ሂደት መሪው ከበላይ ሃላፊው ጋር በመነጋገር ከሌላ የስራ ሂደት እንዲመደብ ያደርጋል፡፡ በዚህ መሰረት ኮሚቴው የከተማ አስተዳደሩን የመንግሥት የግዥ አዋጅና መመሪያ መሠረት በማድረግ ጨረታውን ይገመግማል የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣ ኮሚሽኑ ከጨረታ ሂደት እና ከውል አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ይገመግማል ክትትል ያደርጋል፣

# የቀጠለ...

4) ውስብስብ ለሆኑና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚፈልጉ ግ¡ዎች ጊዜያዊ የቴክኒክ ገም ጋሚ ኮሚቴዎች እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡

5) የወረዳ የፋይናንስ ፣ የንብረት አስተዳደርና ግዥ ተወካይ የሚቀርቡ የግዥ ጥያቄዎችን በሕዝብ ተሳትፎና ዕቅድ ተወካይ በኩል የተደገፉ መሆናቸውን በማረጋገጥ በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መስረት በወረዳው ካውንስል የፀደቀበትን ቃለ-ጉባዔ በመያዝ ለዕቃው ወይም ለአገልግሎቱ ግዥ ክፍያ ይፈጽማል፡፡ ክፍያ የተፈጸመባቸውን ሰነዶችን በአግባቡ ይይዛል፣ይጠብቃል፣

6) ለቅጥር ለጥበቃ ወርሀዊ ደሞዝ ክፍያን በተመለከተ ከ"A" አካውንት ወጭ በማድረግ ክፍያ እንዲፈፀምላቸው

አመሰግናለሁ!